በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
National Archives and Library Agency

# መዝገበ ህትመት ዳሰሳ
# Analytical Biblography

**ቅፅ 25፣ ቁጥር 5፣ 2000 ዓ.ም. Vol. 25, No. 5, 2008**

በሕትመት ማግኛና ዩኒየን ካታሎግ መምሪያ
በናሽናል ቢብሊዮግራፊ ቡድን ተዘጋጀ

**Prepared by**
**Union Catalogue and Acquisition Department**
**(National Bibliography Team)**

ሚያዝያ 2000
**April 2008**

# የአርዕስት ማውጫ


ርዕስ ገፅ

1. ክፍል አንድ (ዕትም ያልሆኑ)
   1. ሃይማኖተ አበው……………………………………………………..1
   2. መልክዓ ጉባዔ …………………………………………………....1
   3. መፅሐፈ ሐዊ……………………………………………….......1
   4. መፅሐፈ ሐዲሳት …………………………………………….2
   5. መፅሐፈ ምስጢር…………………………………………….2
   6. መፅሐፈ ስንክሳር …………………………………………..….2
   7. መፅሐፈ ብሉያት …………………………………………….3
   8. መፅሐፈ ድጓ ……………………………………………………..3
   9. ዳዊት …………………………………………………………..4
   10. ግብረ ህማማት ……………………………………………….4
2. ክፍል ሁለት (ዕትም የሆኑ)
   1. አክሲማሮስ ሃይማኖታዊ የሥነ ፍጥረት መፅሐፍ ………………….5
   2. ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ …………………………………………6
   3. ዳዊት …………………………………………………………….7
   4. ጦቢያ ……………………………………………………………7
   5. ወዳጄ ልቤ ……………………………………………………….8
   6. መንግስትና የህዝብ አስተዳደር ………………………………..…8-9
   7. ጎበዝ አየን………………………………………………….....10
   8. አርአያ ……………………………………………………….....10
   9. ዝክረ ነገር ……………………………………………………11
   10. እንደወጣች ቀረች ……………………………………………11-12

11. የግብፅ፣ የሳባና የኢትዮጵያ ፊደሎች ማስታወሻ.....................12

12. አርሙኝ ....................................................................13

13. የሾህ አክሊል ............................................................13

14. ውብ ነበረች ..........................................................13-14

15. አልወለድም ...............................................................14

16. የዓመፅ ኑዛዜ .............................................................15

17. ፍቅር እስከ መቃብር ......................................................15

18. የመኖርን ትርጉም ገለጠልኝ ወንድም ...................................16

19. አግዐዚ ......................................................................17

20. አደፍርስ ....................................................................17

21. እሳት ወይ አበባ ..........................................................18

22. የተውኔት ጉባዔ ...........................................................18

23. ከአድማስ ባሻገር ..........................................................19

24. የታንጉት ምስጢር .........................................................19

# ክፍል አንድ
# የጥንታዊ ጽሑፍ ክፍል
# (ዕትም ያልሆኑ)

## ግብረ ሕማማት

በሕማማት ሰሞን በወርኃ ጾም በመጨረሻው ሣምንት የሚነበብ ከኦሪት፣ ከነቢያት፣ ከመዝሙረ ዳዊት፣ ከአርባዕቱ ወንጌል፣ ከሃይማኖተ አበው የተውጣጣና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገውን ታምርና የደረሰበትን መከራ የሚናገር መጽሐፍ ነው።

## መልክዓ ጉባዔ

ይህ መፍሐፍ የተለያዩ የቅዱሳንን፣ የጻድቃንን እና የመላእክትን ምሥጋናና ክብር፣ መንፈሣዊ ፍቅር የሚገልጽ መልክዓ መልኮች አንድ ላይ ተሰባስበው የሚገኙበት ነው።

## ሃይማኖተ አበው

ቀደም ባሉት ጊዜያት በሃይማኖት ላይ የተደረጉ ክርክሮችን አጠቃሎ ይዟል። የሥላሴዎች ሦስትነትና አንድነት፣ ጥምቀትንና የቁርባንን ጥቅም አስመልክቶ የተሠጡ የተለያዩ አስተያዩቶችን ከማተቱም በተጨማሪ፣ በእነዚህ ክርክሮች ሰለሥቱ ምዕት ከአርዮስ ጋር፣ መቶ ሃምሳው ከመቅደንዩስ ጋር ፣ ሁለት መቶው ከንስጥሮስ ጋር ገጥመው የየራሳቸውን የሃይማኖት ልዩነት ያንፀባረቁበትን አስተያየት ያካተተ መጽሐፍ ነው።

## መጽሐፈ ሐዊ

መምህር አንቲኮስ የሚባል የሃይማኖት አባት ከቅዱስ መጻሕፍት ማለትም ከብሉይና ከሀዲስ ኪዳን፣ ከመጻህፍተ ሊቃውንት ሀሳቦችን ሰብስቦ የጻፈው ነው:: መጽሐፉ ሥጋዊና መንፈሳዊ ምክር የያዘ ሆኖ እናገኘዋለን::

## መጽሐፈ ስንክሣር

ትርጉሙ ጉባዔ ማለት ሲሆን መምህርና ቤተክርስቲያን፣ አባ ሚካኤል ኤጲስ ቆጶስ ከሀገረ አትሪብ ወመሲግ፣ አባ ዩሐንስ ኤጲስ ቆጶስ ዘሀገረ ቡርልስ እና ሌሎች ቅዱሳን ከጻድቃን፣ ከሐዋርያት፣ ከሰማዕታት ገድል፣ የመላእክትንና የነቢያትን ገቢረ ተዓምራት እንዲሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስላደረገው ተዓምራት ሥራ እንዲታሰብ ገድላቸውም በየእለቱ እንዲነበብ አውጣጥተው የጻፉት ነው::

## አሥርቱ ወክልኤቱ አእናቁ

ዕንቁ በተለያዩ መጻሕፍት የተለያየ መጠሪያ ስም እንዳለው ይናገራል:: በመቀጠልም ስለሚዛን ማለትም ወቄት ስለ ድሪም በውስጡ ተፅፎ ይገኛል:: የእሥራኤል ነገሥታትን ስምና የገዙበትን ዘመን፣ የነቢያትን ነገድ፣ አገራቸውን፣ ትንቢታቸውን፣ የመታሰቢያ ዕለታቸውን፣ እንዲሁም የሐዋርያትን ስምና ትውልድ የሰባ አርድዕትን ሥራ ይተርካል:: በተጨማሪም የጠዋትና የማታ የፀሎት ሥርዓትን ያስተምራል::

## መጽሐፈ ድጓ

ታላቁ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ከመፃሕፍተ ብሉያትና ከመፃሕፍተ ሐዲሳት እንዲሁም ከመፃሕፍተ ሊቃውንት አውጣጥቶ በሦስት የዜማ ስልቶች ማለትም ግዕዝ፣ ዕዝል፣ አራራይ በመባል የሚታወቁትን የዜማ ዓይነቶች የያዘ መጽሐፍ ነው፡፡ ያሬድ በአምስተኛው መቶ ዘመን የነበረ ሲሆን አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች ግን በአራተኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ እንደነበረ ይገልጻሉ፡፡ በድጓ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት እነዚህ ዜማዎች ለቤተክርስቲያን መገልገያነት ይውላሉ፡፡

## ዳዊት

የክርስትና ዕምነት ተከታዮች ለፀሎት የሚጠቀሙበት ሲሆን በውስጡም ጠቃሚ ትምህርቶችና ምክሮች ይገኙበታል፡፡ ዳዊት በሕይወት ሳሉ ብቻ ሣይሆን ለሙትም በዕለተ ሞቱ ጊዜ የክርስትና ስሙን በማስገባት ይደግምለታል፡፡ በሕይወት ዘመን የሚጸለየው ለሥጋ በረከት ለነፍስ ደኀንነትን እንደሚሰጥ ስለሚታመንበት ነው፡፡

## መጽሐፈ ብሉያት

ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ሚልክያስ ያለውንና ኦሪቱን ክፍል ብቻ የያዘ መጽሐፍ ሲሆን በዝርዝር ስምንት ብሔረ ኦሪት፣ አስራ አምስት ደቂቀ ነቢያት፣ መቃቢያን ን፣ ኩፋሌን፣ ጨምሮ እነዚህንና የመሳሰሉትን በጥቅሉ ሲቆጠር 46 መጻሕፍተ ብሉያትን በነጠላው ደግሞ 2 መጻሕፍተ ብሉያትን አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡

## መጽሐፈ ሐዲሳት

ከማቴዎስ ወንጌል እስከ ራዕየ ዮሐንስ ያለውን አጠቃሎ የያዙ መጻሕፍት ሲሆኑ ቀደም ሲል ነቢያት በተናገሩለት ትንቢት መሰረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ስለ ሰው ልጆች ያደረገውን ገቢረ ተዓምራት፣ የተቀበለውን መከራ፣ ያስተማረውን ትምህርት የሚያሳዩ፣ ዳግም ወደ እዚህ ዓለም እንደሚመጣ የሚያስረዱ መጻሕፍት ናቸው። በተጨማሪም መጽሐፈ ኪዳንን፣ ስርዓተ ፅዮንን፣ ሲኖዶስን፣ ቀሌምንጦስን ፣ ዲዲስትሪያንን አጠቃሎ 35 መጻሕፈተ ሐዲሳትን ያየዘ ነው።

## መጽሐፈ ምሥጢር፣

በኢትዮጵያዊው ሊቅ አባ ጊዮርገስ ዘጋስናል የተደረሰ ነው። ይህ መጽሐፍ ከተለያዩ መጽሐፍት የተሰበሰበ የሃይማኖት ምክርና ተግሣፅ ያለበት፣ ለልደት፣ ለጥምቀት፣ ለቃና ዘገሊላና ከጾመ አርባ አንስቶ እስከ እርገት ድረስ ቤተክርስቲያን በፀሎትነት የምትገለገልበት፣ እንዲሁም ስለ ሥላሴ አንድነትና ሦስትነት ስለ ወልደ እግዚአብሔር ሥጋ መልበስ የሚናገር ሆኖ እናገኘዋለን።

# ክፍል ሁለት
# እትም መጻሕፍት

## አክሲማሮስ ፡-
## (ሃይማኖታዊ የሥነ ፍጥረት መጽሐፍ)

ኢጲፋንዮስ የተባለው የቆጵሮስ ኤጲስ ቆጶስ የፃፈው መፅሐፍ ሲሆን፣ አክሲማሮስ ማለት ስድስት ቀናት ማለት ነው፡፡ ስለ ስድስት ቀናት ማለትም ከዕለተ እሁድ እስከ ዕለተ ዐርብ ያለውን ሥነ ፍጥረት ዝርዝር የሚገልጽና ከፅርሐ አርያም እስከ በርባሮስ ድረስ ያለውን ፍጥረት ሁሉ አፈጣጠርና አቀማመጥ የሚያስረዳ ታላቅ የሥነ ፍጥረት መፅሐፍ ነው፡፡

በዚሁ መሠረት እግዚአብሔር ዘላለማዊ የሆነ፣ ዓለም ሳይፈጠር ብቻውን የነበረ፣ ወሰን፣ ጥንት፣ ፍፃሜና ምሳሌ የሌለውና በዓለም የሞላ መሆኑን ይገልፃል፡፡

ስለመጀመሪያ አፈጣጠር ሲናገር እግዚአብሔር ይሁን አለ እሳት፣ ነፋስ ውሃና መሬት ተገኙ፡፡ ይህም በእግዚአብሔር ሀይልና ጥበብ ነው እሳትን ፈጥሮ ብቻውን አላደረገውም፣ ከእሳቱም መላዕክትን ፈጠረ፣ ከነፋሱም የነፋስን አርአያ ከውሃውም አዕዋፋትንና አሦችን አወጣ፣ ከመሬት ደግሞ አራዊትና ሥጋ የለበሱ ተንቀሳቃሾችንና ዕፅዋትን ፈጠረ፡፡

እግዚአብሔር መጀመሪያ እሳትን ባረከው፣ አለውም ብዛ ተባዛ እግዚአብሔር እንዳዘዘውም እሳት ተባዛ ተስፋፋ እግዚአብሔር እንደ ፈቀደውም ሆነ እግዚአብሔር ከወሰነውም እንዳያልፍ ሆነ፡፡ እግዚአብሔር መኖሪያውን በእሳት ላይ አደረገ እግዚአብሔር በሁለም ቦታ የሚገኝ የማይወሰንለትና ቦታ የማይወስነው በሁሉም ገጽ ያለ ነውና እያለ የሚቀጥል ሲሆን፣ ከዚህም በተጨማሪ ከሰላሳ ስድስት በላይ የሚሆኑ ስለ ተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች የሚያወሱ ክፍሎች አሉት፡፡

# ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ

ይህ መፅሐፍ በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ብሎ ይጀምርና በእግዚአብሔር አጋዥነት የቀድሞ አባቶችን ዜናና የነገስታትን የግዛታቸውን ዘመን አቆጣጠር የያዘውን የታሪክ መጽሐፍ ከአዳም እስከ እስራኤል ንጉሥ መጨረሻ ያለውን የግብፁ የክርስቶስ ወገን የሆነው ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ ያዘጋጀውን እንጀምራለን ይላል፡፡

አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ናቸው፣ በመለኮት አንድ በአካል ሦስት፣ በጥበቡ ሃያል የሆነ ነው ብሎ ይህንን መፅሐፍ ፈልጎ ያገኘው የእግዚአብሔር ወዳጅ የሆነውና ስመ መንግስቱ ቆስጠንጢኖስ የተባለው ዘርዓያቆብ መሆኑን ይገልፃል፡፡ መፅሐፉ የቅዱሳን ሐዋርያትን፣ የሊቃነ ጳጳሳትንና የክርስቲያን ነገስታትን ታሪክ ይናገራል፡፡

ስለ አለም አፈጣጠር ሲናገርም ስለ አለም አፈጣጠር ፈላስፎች አልተስማሙም ይህ ዓለም ረጅም ዘመን የቆየ አንደፈጣሪው መጀመሪያ የሌለው መጨረሻም የሌለው ፍጡርም ከፈጣሪው ጋር አይለይም የዚህ ፍልስፍና ተከታዮች ( አመንጪዎች) አርስጣጣሊስና የሱ ተማሪ የሆነው የፊሊጶስ ልጅ እስክንድር ዮናናዊ እና አፍላጦን ከቀደምት ፈላስፋዎች ውስጥ ነበሩ፡፡ የዓለምንም አፈጣጠር በእግዚአብሔር አጋዥነት ከኦሪትና ከነቢያት መፃሕፍት እንረዳለን፡፡

ስለ ዘመን አቆጣጠር ከማይስማሙ ሰዎች መካከል በጥንት ዘመን አልነበረም የሚሉ አሉ፡፡ በሌላ በኩል አልተፈጠረም፣ አይለወጥም፣ መጨረሻም የለውም የሚሉ አሉ፡፡ ሌሎች ፍጥረታት ግን ይለወጣሉ፣ ይጠፋሉ ይላሉ፡፡ እኛ ግን ዓለም በዕውነት ተፈጥሯል እንላለን እያለ ይቀጥላል፡፡

ስለዘመን አቆጣጠርና ከእርሱ ስላለው የዓለም መፈጠርና የዘመን አቆጣጠር መጀመሪያና መጨረሻ ያለው መሆኑን ከመፃሕፍት አወቅን ፡፡ በዚህም ጊዜ ቁጥር እንዳለው ተረዳን፡፡ ነገር ግን ሁሉም በጊዜው ይለወጣል ከዚህ በኋላ የክዋክብት አቆጣጠር ይታወቃል፡፡

የዘመን ጭማሪው ከመጀመሪያው ከክዋክብት አካሄድ ወደ መስኮተ ሀመል መግባት ይጀምርና እስከ 762 ዓመት 4000፣ 300 000፣ 20,000፣ 361 ዓመትና ከ7 ወራት ከ12 ዕለት ነው፡፡ ከአዳም እስከ ምፅዐተ ክርስቶስ 5500 ዓመት ነው፡፡ ይህንንም በአግዚአብሔር ረዳትነት እናስረዳለን ሲል ያብራራዋል፡፡

## ዳዊት

ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ፊደል በ1513 እ.ኤ.አ. የታተመ ነው፡፡ በትውልድ ጀርመናዊ የሆኑት ዩሐንስ ፖትኪን በ1513 እ.ኤ.አ. ያሣተሙት ይኸው መጽሐፍ በወቅቱ ቫቲካን ከሚገኘው ቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም ይኖሩ ከነበሩት ኢትዮጵያዊ አባ ተስፋ ጽዮን ( በ16ኛው ምዕተ ዓመት የኖሩና በ1550 እ.ኤ.አ. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው በዚያው በቫቲካን ቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም የተቀበሩ ናቸው) የግዕዝን ቋንቋ በመማርና የኢትዮጵያን ፊደል በማስቀረጽ የተፃፉእንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ መጽሐፉ የሕትመት ሥራ በተጀመረ 60ኛ ዓመት ላይ የታተመ በመሆኑ በዓለማችን ቀደም ብሎ ከታተሙት ጥቂት መጽሐፎች ውስጥ አንዱ ሊሆን በቅቷል፡፡

## ጦቢያ

ይህ መፅሐፍ በአፈወርቅ ገ/እየሱስ በ1900 ዓ.ም. በሮም ከተማ ታተመ፡፡ መፅሐፉ 90 ገጾች አሉት፡፡

በኢትዮጵያ የሥነ ፅሑፍ ታሪክ የመጀመሪያ ልብወለድ መፅሐፍ ለመሆኑ የሚነገርለት ይህ መጽሐፍ በወቅቱ ተነስቶ የነበረውን የአረማውያንንና የክርስቲያኖችን ጦርነት ይተርካል፡፡ ደራሲው በመፅሐፍ ውስጥ ስለተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ማለትም ስለደግነትና ክፋት፣ ስለሀይማኖትና ፍቅር በሰፊው ያትታሉ፡፡ መፅሐፉ በተለይ የፍቅርን ሀያልነት ለማሳየትና የሀይማኖት ልዩነት ስላልበገረው ታላቅ ፍቅር በሰፊው ይተርካል፡፡ በተጨማሪም ደራሲው በጽሐፉ ውስጥ ሊያስተላልፉ የሞከሩት መልዕክት የሰው ልጅ በባዕድ አምልኮ ተሸብቦ ከመኖር ይልቅ ፈተናና ችግር ቢገጥሙት እንኳን ለእነዚህ ሳይበገር በአንድ አምላክ አምኖ ከጸና ድል ሊያደርግ እንደሚችል ነው፡፡

## ወዳጄ ልቤ

ብላታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ በ1915 ዓ.ም. ለህትመት ያበቁት ይህ መጽሐፍ ዓለማዊ ሃይማኖትን ማስተማሪያ ሲሆን፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ምሣሌዎችን በመጥቀስ ክፋት የሰው ልጆች አጥፊና መጨረሻው የማያምር መሆኑን ያስረዳል። ከቀድሞው የሃይማኖት ትምህርት ለየት ባለ ልብ ወለድ መልክ የቀረበ በመሆኑ ብዙ አንባቢዎችን እንደ አረካና ጥሩ የጊዜ ማሳለፊያ እንደነበር ይታወቃል።

## መንግስትና የሕዝብ አስተዳደር

በቢትወደድ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ በ1916 ዓ.ም. ተጽፎ ለህትመት የበቃው ይህ መጽሐፍ ከመስራት የተነሳ የሰው ልጅ እንዴት ከተፈጥሮ ጥገኝነት ተላቅቆ ከኋላ ቀር አኗኗር ወደ ተሻለ ሕይወት እንደሚለወጥ የሚያስረዳ ሲሆን የዓለም ሕዝቦች የዕውቀታቸውና የሀብታቸው ደረጃ ከፍና ዝቅ ያለ መሆኑ ምክንያቱ ከጦርነት የተነሳ ነው ይላል። ጦርነቱንም የሚያነሡ ነገስታትና አለቆቹ ሁሉ ልባቸው ሀብት እንደፈለጉ አይገልፅም። ነገር ግን ስም ለመፈለግና ለማግኘት ወይም ሀይማኖቱን ለማስፋፋት ወይም የተጠቃውን ለመርዳት አስመስለው ይነሳሉ። የጦርነት ሁሉ ፍፃሜ ምኞት ግን መዝረፍና ማስገበር ነው። ይህንንም ስል ዕውቀታቸው የሰፋ ነገስታትም ቢሆኑ መዝረፍን አይተውም። አዘራረፋቸው ግን የዕውቀት አዘራረፍ ነው እያለ በሰፊው ያወሳል።

በአክሱም ዘመነ መንግስት የእስራኤልና የአህዛብ ወገን ተብሎ የሁለት ዓመት ጦርነት በመፍጀቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍ ወዳለው ደረጃ እንዳይደርስ ዋና መሰናክል ሆኗል።

ዋጋ ማለት የስራ መለኪያ ነው። ዕውቀት ከጉልበት ይከበራል ዕውቀት የሌለው ሕዝብ ሁሉ ለብቻው መንግስት ቢኖረውም ባይኖረውም ዕውቀት ያላቸው ሕዝቦች ይገዙታል። ሰው ሲፈጠር ጌታና ድሀ ሆኖ አልተፈጠረም ድህነትና ጌትነት የተለየው በሰው ዕውቀት ነው። የሀብት መለኪያ ሥራ ነው ስለዚህ ሀብት ማለት የተከማቸ ሥራ ማለት ነው።

አርነት ያለው ሕዝብ ማለት ዕውነተኛ ትርጉሙ ለብቻው መንግስት ያለው ማለት ብቻ አይደለም ራሱንም የቻለ ሕዝብ ማለት ነው እንጂ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ እስከዛሬ ድረስ ገና ራሱን አልቻለም:: እስቲ የሰራነውን እንይ እንዴት የተሠራና ማን ያመጣው ነው? ጭቅጭቅና ጦር ቅድሚያ የሚበዛው በስራ ባልሰለጠኑ ሕዝቦች ውስጥ ነው:: ስለዚህም ሕዝቡ ሲሰለጥን የሹሞቹን ዕርዳታና ቸርነት የሚፈልግበት ምክንያት ሁሉ ያንሳል::

ሕዝቡ እንዲረዳና እንዲበረታ የፈለገ መንግስት ከሁሉ ነገር በፊት የባላገሩ ትዳር እየተሻለ እንዲሄድ መጣር አለበት:: ስለዚህ የሕዝብ ማሠልጠኛ ት/ቤቶች በየዐይነቱ ማቋቋም፣ ሕዝቦችን የሚያቀራርብ የትራንስፖርት መንገድና ምድር ባቡር መስራትና የውጭ ኢንቨስተርን በደስታ ተቀብሎ ማስተናገድ፣ እነዚህን ከተከተለ የመንግስት ሀብትና ሀይል እያደገ ይሄዳል ብለው በመቀጠልም ስለ ትምህርት ጥቅም ሲጽፉ ትምህርት በሌለበት ሀገር ለስርዓት የሚሆን መሠረት አይገኝም ስርዓት የሚገኘው በትምህርት ነውና ትምህርት የሌለው ሕዝብ ስርዓት አይወድም አይጠቅመውም በማለት ያብራራሉ::

ስለገንዘብ አጠቃቀምም ደግሞ ሲጽፉ ሕዝቡ ገንዘቡን በቤት ውስጥ ከማስቀመጥ በባንክ አስቀምጦ በባንክ ኖት መጠቀምን መልመድ አለበት:: የባንክ ስራ በሞኖፖል መሆን የለበትም ለደሀ ሕዝብ ከትልቁ የለውጥ መሳሪያ ይልቅ ትንንሹ የለውጥ መሳሪያ ያስፈልጋል (ከ.ሩብ፣ ከአለድ እና ከብር በመተመን መገዛዛትን ይሻል):: የኢትዮጵያ መንግስት የለውጥ መሳሪያ ወርቅ እንዲሆን ቢጥርበትና እንዲሁም የገንዘብ ደንብ ማውጣት አለበት በማለት የደንብን አስፈላጊነት በጽሁፋቸው ይገልጻሉ::

# ጉበዝ አየን

በዘመናቸው ዕውቅ የሥነ ጥበብ ሰዎች አንዱ ከነበሩት ዮፍታሔ ንጉሤ ተደርሶ በዓ.ም. ለህትመት ፡፡ በጐጃም ክፍለ ሀገር በደብረ ኤልያስ ቀበሌ በ1897 ዓ.ም. ተወልደው ባልታወቀ ምክንያት ሰኔ 30 1939 ዓ.ም. ሌሊት ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት እኚህ ታላቁ ሰወ በርካታ ድርሰቶችን የጻፉ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች አብዛኛዎቹ ለሕትመት አልበቁም፡፡ ከጽሑፎቻቸውም ውስጥ ለሕትመት የበቃው ጉበዝ አየን የሚለው መጽሐፋቸው ሲሆን በመጽሐፉ ተጠቃሎ የሚገኘው ፍሬ ሃሳብ የ1928 የጣሊያንን ወረራ አስመልክቶ ሕዝቡ በጀግንነት እንዲጋፈጠው የሚያበረታታና የሀገር ፍቅር ስሜትን የሚቀሰቅስ ነው፡፡

# አርአያ

በፈረንሣይ ሀገር ከፍተኛ ትምህርት ተምሮ ወደ ሀገሩ የተመለሰው አርአያ (የታሪኩ ባለቤት) የተማረውን ትምህርትና ያየውን ሥልጣኔ በሀገሩ በሥራ ላይ ለማዋል መሞከሩን ይተርካል፡፡

ሆኖም ግን ይህ ሙከራ በአንድ በኩል በአካባቢው የነበረው የባህልና የልምድ ተፅዕኖ ከእሱ የሠለጠነ አስተሳሰብ ጋር በመጋጨቱና በኢጣሊያ ወረራ ምክንያት ያሰበው ሳይሳካለት እንደቀረ ያወሳል፡፡ ከዚህም በላይ ስለ ማይጨው ጦርነትና የጦርነቱን ሂደትም ይዘግባል፡፡ ይህ ታሪካዊ ልብወለድ መጽሐፍ በደጃዝማች ግርማቸው ተክለሐወርያት ተደርሶ በ1941 ዓ.ም. ለህትመት የበቃ ነው፡፡

# ዝክረ ነገር

በብላቴን ማንተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል ተጽፎ በ1942 ዓ.ም. ለህትመት የበቃው ይህ መጽሐፍ በታሪክ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠውና አጠቃላዩን የኢትዮጵያን ሕዝብ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ የሚዘክር ነው::

# እንደወጣች ቀረች

ይህ መፅሐፍ 189 ገጾች ያሉትና በ1946 ዓ.ም. የተፃፈ ሲሆን በውስጡም ከ1928-1933 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ላይ የተፈፀመው የኢጣሊያ ወረራና በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ያመጣው አያሌ ቀውሶች በሰፊው ያትታል:: በተለይም በህዝቡ መንፈስ ላይ፣ በአገሪቱ ልማድና የኑሮ ባህል ላይ ባጠቃላይ በማህበራዊ ህይወቱ ላይ ታላቅ ቀውስን ያስከተለ መሆኑንም ያብራራል::

የነበረውን የጦርነት አስከፊነት መፅሐፉ ሲያትት ኢጣሊያኖች እጅግ ጨካኞች ነበሩ:: በተለይም ከሀገሬው ተወላጆች በልዩ ልዩ ምክንያት በዘመኑ በእስር ላይ የነበሩትን በመፍታት ለራሳቸው ባንዳ አድርገው ከመለመሏቸው በኃላ ከአርበኞች ጋር ያዋጓቸው ነበር ሀገሬውን እርስ በርሱ በማዋጋት ህዝቡን ጨርሶ ሀገሪቷን ለመውረስ ከፍተኛ እቅድ ነበራቸው:: አርበኞች ግን የምግብ ችግር፣ የክረምቱ መጫንና የበረሀው ኑሮ ሳያግዳቸው ቤት ሀገር ነው ሀገር ከሌለ ቤት የለም በማለት ለባዕድ መገዛት አሻፈረኝ ብለው ለነፃነታቸው በየዱሩ እንደተዋጉም ያወሳል::

ፀሀፊው በመፀሐፉ በሰፊው ሊያሳይ የሞከረው ሀሳብ በኢጣሊያ ወረራ ምክንያት በሀገሪቱ የተስፋፋውን የሴትኛ አዳሪነት አስከፊ ህይወት ነው::

ይህ ዘመን የሰው ስብዕና የተዋረደበት፣ ገንዘብ ከሰው ይልቅ የተወደደበት፣ ፍቅርና ዘመድ ወደ ገንዘብ የተለወጠበት ዘመን ነበር:: ከዚህም የተነሳ በከተማ ሲኖር ባለትዳር ከመሆን ይልቅ ሴትኛ አዳሪ መሆን ሰፊ ነፃነትና ደስታም ያለበት ኑሮ ነው ተብሎ የታመነበት ዘመንም ነበር::

ሌላው የማህበራዊ ኑሮ ቀውስ ነው ብለው ፀሐፊው በስፋት ያተቱት ስለመጠጥ ጠንቅ ነው:: በአጠቃላይ ደራሲው ይህንን ሁሉ የማህበራዊ ህይወት

ቀውሶች ያመጣው የኢጣሊያ መምጣት ነው፡፡ ላይጠቀምበት የሰው ሀገር ወሮ ፣ የሰውንም ቤተሰብ በትኖ፣ የሰውንም ትዳር አጥፍቶ፣ የሰውንም ምግባር አበላሽቶ ከፈላስፋዎች መካከል ዓለም እንደ ፈጣሪው የመጀመሪያው ነው፡፡ መጀመሪያና መጨረሻ የለውም ፍጥር ከፈጣሪው አይለይምና ይህም አባባል የፈላስፋው የአርስጣጣሊስ ሲሆን ከእርሱ በኋላ የፊሊጶስ ልጅ የእስክንድር፣ ሴቶቹንም ቅጥ በሌለው ኑሮ ዕድሜያቸውን እንዲጨረሱ አደረጋቸው በማለት ሴተኛ አዳሪነትን በእጅጉ የሚቃወም ሲሆን በተጨማሪም ከዚህ በፊት ይህ ምግባር (ሴተኛ አዳሪነት) ከነውር ይቆጠር ነበር ነውርነቱ የተሻረው በኢጣሊያኖች ጊዜ እንደሆነ ስለተረዳሁ ለወገኖቼ ይህንን የመሰለ ኑሮ የማያዘልቅ ስለሆነ አዲሶቹም እንዳይታለሉ የገቡትም ወደ ወትሮው ትዳራቸው እንዲመለሱ የሚሻል ነው በማለት ይህንን ልብወለድ መፅሐፋቸውን መታሰቢያነቱ ለኢትዮጵያውያን ሴቶች እንዲሆን በማበርከተት ፅፈዋል፡፡

## የግብፅ የሳባና የኢትዮጵያ ፊደሎች ማስታወሻ

ግዕዝና አማርኛ በተቀረው የዓለም ክፍል እንዲታወቅ ጊዜአቸውን መስዋዕት በማድረግ ለደከሙ የውጭ አገር ሊቃውንት መታሰቢያ ይሆን ዘንድ በታሪክ ተመራማሪው አቶ ተክለጻድቅ መኩሪያ የተጻፈው ይህ መጽሐፍ ለህትመት የበቃው በ1950 ዓ.ም. ነበር፡፡ መጽሐፉን ከሌሎች መጻሕፍት ለየት የሚያደርገው ዛሬ በአገራችን ውስጥ የማይታወቁትን ፊደላት በደራሲው ጥረት በእጅ ተጽፈው ፎቶግራፍ ከተነሱ በኋላ ለህትመት መብቃት ነው፡፡

## አርሙኝ

ይህ መጽሐፍ ደራሲው ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው በ1952 ዓ.ም. ለህትመት ያበቁት ሲሆን፣ የሕይወት ታሪካቸውን ባጭሩ እንዲሁም በተለያየ ጊዜ የሠሩዋቸውን ልብ ወለድ ስብስቦችን፣ ስለ ማይጨው ጦርነት እና የዓለም ፖለቲካን በማካተት የጻፉትን ጠቅልሎ የያዘ ነው፡፡

# የሾህ አክሊል

በዕውቁ ባለቅኔና ደራሲ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድኅን በ1952 ዓ.ም የተደረሰው ይህ ተውኔት በመኳንንት ቤት ያደገ አንድ ወጣት የመኳንንት ሴት ልጅ ለትዳር መፈለጉንና እሱ ግን አቻ ቤተሰብ ባለመሆኑ በጋብቻው ብቁ ሳይሆን እንደቀረ ያሳያል፡፡ ይኸውም አንድ ሰው ማንነቱ የሚረጋገጠው በእሱ በራሱ ሣይሆን በቤተሰቡና በወገኑ እንደነበር የሚያመለክት ነው፡፡

# ውብ ነበረች

ይህ መፅሐፍ በሰይፈ ሚካኤል የተሻወርቅ በ1953 ዓ.ም.የተፃፈ ሲሆን በአዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ቤት ታትመ በውስጡም 50 ገጾች አሉበት፡፡
« ውብ ነበረች» የምታወሳው ያንዲት « አልማዝ » ተብላ የተሰየመች ውበ ሴት ሙሉ የህይወት ታሪክ ነው፡፡ የመፅሐፉ መጠሪያ ስም ሆኖ የተጠቀሰው
« ውብ ነበረች» የተባለው ንዑስ አንቀፅ ባለታሪኳ እስከ ጊዜ ሞቷ ስታስታውሰው የኖረችው ወዳጅዋ የነበረው መልከ መልካም ወጣት ጎረምሳ ኮብልሎ ጠፍቶባት ሲመለስ በመጎሳቆሏ ረስቷት ወርውሮባት የሄደው ንግግር ነው፡፡

ይህች መጽሐፍ አብዛኛውን ለሴቶች ምክር የምትሰጥ ናት ምክንያቱም ባለታሪኳን አልማዝ እዚያ ሁሉ ሥቃይና አሰቃቂ ሞት ያደረሳት ያላቻ ጋብቻና በዘመኑ ገንዘብ ለማግኘትና ለመከበር መንገድ ነው የተባለው የሴተኛ አዳሪነት ኑሮ ነው፡፡

ይህች መጽሐፍ የተለያየ ምክርን የየዘች ሲሆን፡፡ አልማዝ ጋሻዎቼ ናቸው ብላ የምትተማመንባቸው ወላጆችዋ ሳታስበው ዕድሜዋም ሳይደርስና የጋብቻ ስሜት ሳይኖራት ታቅፎ ላሳደጋት አባቷ መሆን ለሚችል ሰው ለስማቸው ሲሉ ሳይወዱ በግድ ቃላቸውን ለማክበር ዳሯት፡፡ በዚህም ምክንያት በመኮብለሏ በሁለቱ ቤተሰቦች ምን ችግር እንደደረሰባቸው ለወላጆች ታስረዳለች፡፡ ሊወልዳት ለሚችል ሰው መዳር ልጅን ማሰቃየት እንደሚሆን በሰፊው ታስተምራለች፡፡
እንዲሁም በዘመኑ ተስፋፍቶ የነበረው የሴትኛ አዳሪነት ኑሮ እንዴት ቤተሰብንና ትዳርን ይበትን እንደነበረና ይጠቅመናል ብለው የያዙትንም ሴቶች በመጨረሻ ለሞት ይዳርጋቸው እንደነበረም ትተርካለች፡፡

ከነዚህም የመጀመሪያው ምዕራፍ በባለታሪኳ መኮብለል ምክንያት ሁለቱም ቤተሰቦች ላይ የደረሰውን ችግር የተወራበት ሲሆን ሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ በመደለል ከደህና ንብረቷ መፈናቀሏን የሚያወሳው ክፍል ነው፡፡ ከዚህ በኋላ በተርታ ያሉት ሦስት ምዕራፎች የሚተነትኑት ያባበሏትን ሴት ህይወት በማደስ ባለታሪኳ እንዴት የራሳዋ ወርቃማ ጊዜ እንዳባከነባት ሲሆን የመጨረሻዎቹ ሁለቱ ምዕራፎች ደግሞ እስከ ጊዜ ሞቷ የነበረባትን ከባድ የኑሮ ትግል ነው፡፡

## አልወለድም

በደራሲ አቤ ጉበኛ ብዕር ተከሽኖ የቀረበና በ1955 ዓ.ም. ለሕትመት የበቃ ልብ ወለድ መጽሐፍ ነው፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ ማንኛውም ሰው ከእናቱ ማህፀን ጀምሮ ምቾትና ጥንቃቄ ሊለየው እንደማይገባ የሚያትት ሲሆን በመታየት ላይ ያለው እውነታ ግን ለቁጥር አዳጋች የሆነ የሰው ዘር በድህነት ተወልዶ በድህነት አድጐና ኖሮ በድህነት እንደሚያልፍ ያሳያል፡፡ እንዲህ ያለው ሁኔታ አግባብ አለመሆኑን የሚቃወመው ይኸው መጽሐፍ የሰው ልጅ የሚደርስበትን መከራ በመቃወም ይሞግታል፣ የሰው ልጅ መብት በአግባቡ መጠበቅ እንዳለበት ያስረዳል፡፡

## የዓመፅ ኑዛዜ

ይህ መፅሐፍ ከደራሲ አቤ ጉበኛ በ1955 ዓ.ም የተፃፈ ሲሆን 85 ገፆች አሉት፡፡ በመፅሐፉም የተገለፀው ታሪክ ሰፊ ሆኖ ደራሲው ባጭሩ ለመግለፅ ቀላልና አጭር በሆነ ዘዴ የፃፈው ነው፡፡

ታሪኩም አንድ ራሱን ወዳድ ሰው ታሪክ በኑዛዜ መልክ የሚገለፅበት ሲሆን፣ በአንድ የገጠር መንደር ውስጥ ጥሩ ኑሮ አላቸው ከሚባሉ ቤተሰቦች ውስጥ የወጣው ባለታሪክ ቤተሰቦቹን በድንገተኛ ህመም ያጣል፡፡ በድንገትም ያልተጠበቀ የቤተሰብ መበታተን ይደርሳል፡፡ በአጐቱ ሚስት ይፈፀምበት በነበረው ድርጊት ተማሮ ወደ ከተማ የኮበለለው ወጣት ባገኘው የትምህርት ዕድል ተጠቅሞ አገሩንና ወገኖቹን መርዳትና መንከባከብ ሲገባው በተለያዮ ክፉ ነገሮች

ተጠምዶ ይልቁንም በአልጠግብ ባይነት ከሚገባው በላይ ሃብት በማግበሰበስና የወገኖቹንም ድርሻ ጭምር በመሰብሰብ ለአገሩም ሆነ ለወገናቹ የተጣለበትን ተስፋ ሳይፈፅም በሞት አፋፍ ላይ ሳለ የሚሰማውን ፀፀትና እሱን አይተው ሌሎች እንደ እርሱ ከመሆን እንዲቆጠቡ የሚናገርበት ሲሆን በተጨማሪም የርሱ ህይወት ትምህርት እንዲሆናቸው በመጨረሻም ሲበድላቸውና ሲያሳዝናቸው ለኖሩት ወንድሞቹና እንዲሁም ለወገኑ የሚያስተላልፈውን የኑዛዜ ቃል የምናይበት ነው።

## ፍቅር እስከ መቃብር

በ1958 ዓ.ም. የታተመው ይህ ልብወለድ በጊዜው የነበረውን ሥርዓት፣ ወግና ልማድ የሚገልጽ ሲሆን ከሌሎች ልብወለድ ሥራዎች ለየት የሚያደርገው ደራሲው ዶ/ር ሀዲስ አለማየሁ በፊደል አጠቃቀም ላይ ለውጥ አድርገው በማቅረባቸው ነው። ይኸውም ለምሳሌ ያህል ሦስት « ሀ » ዎች ሁለት « ሰ » ዎች ሁለት « አ » ዎች የመሳሰሉትን አንደ አንድ ወይም የመጀመሪያውን ብቻ በመያዝ ነው።

## የመኖርን ትርጉም ገለጠልኝ ወንድም

ይህች መፅሐፍ ከወ/ት አሥራት ታደለ በ1960 ዓ.ም. የተፃፈች ሲሆን 72 ገፆች አሏት።

ይህች መጽሐፍ በውስጧ ብዙ ታሪኮችን በመያዝ «የመኖርን ትርጉም ገለጠልኝ ወንድም» በሚል ርዕስ ለአንባብያን ከብዙ በጥቂቱ ስለ ሰው ልጅ መከራም ሆነ ደስታ ልታብራራ የተዘጋጀች ናት። መጽሀፏ ስለ ትዳር ውጣ ውረድ የምታትት ስትሆን ባለታሪኳ ሴት ዘመናዊ ትምህርት የተከታተለችና በራስዋ ምርጫ እኩያዋንና የሚመጥናትን አግኝታ የተስተካከለ ትዳር ይዛ ለራሷም ሆነ ለሀገሯ ጠቃሚ ዜጋ መሆን እየቻለች በቤተሰቦቿ አስገዳጅነት ወደማትፈልገው ኑሮ ገብታ የስቃይና የመከራ ህይወት በመግፋት ከቆየች በኋላ ትዳሯን ጥላ በመውጣት ወንድሟ ዘንድ በመኖር ያቋረጠችውን ትምህርት ቀጥላ

*ያሰበችው ግብ ለመድረስ መብቃቷን የሚያትት ሲሆን፡፡ በዚሁ ሳታቆም በምርጫዋ የሚመጥናትንና የሚያከብራትን ባል በማግባት ልጆች ወልደው የተደላደለ ኑሮ ለመኖር እንደበቃች ያሳየናል፡፡*

*አንዲት ሴት ትዳር መያዝ ከፈለገች በምንም ዓይነት መንገድ እኩያዋንና ቢጤዋን አታጣም ወንዱም እንደዚሁ፡፡ በሁለቱም ወገን የማያስፈልግ ንትርክ በማብዛት የጋብቻ ክቡርነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መሄድ የለበትም፡፡*

*ሰው ሆኖ ተፈጥሮ ዘወትር ደስ ብሎት የሚኖር የለም፣ በአንደኛው ነገር መደሰት ቢኖር በሌላው ደግሞ መከፋት ይኖራል፡፡ የሰውን ምርጫ ማስገደድ አይቻልም ምርጫው በጋብቻ ብቻ የተወሰነ አይደለም የእያንዳንዱ ሰው ምኞት በጣም የተለያየ ነው፡፡ ሴት ልጅን በማስተማር የተስተካከለ ምርጫ እንዲኖራትና ኑሮዋን በአግባቡ መምራት እንድትችል በተጨማሪም ደግሞ ለሀገሯና ለወገኗ ጠቃሚ አንድትሆን መደገፍና መርዳት ከእያንዳንዱ ዜጋ የሚጠበቅ ግዴታ መሆን እንዳለበት መጽሐፏ ታስረዳለች፡፡*

## <u>አግዐዚ</u>

*ይህ መጽሐፍ በብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ተደርሶ በ1961 ዓ.ም. ለህትመት የበቃ ሲሆን፣ የአንድ ወጣትን ወደ ውጭ ሀገር ለከፍተኛ ትምህርት መሄድና ተምሮም ወደ ሀገሩ በመመለስ ያየውን ሥልጣኔና የተማረውን ትምህርት በሥራ ላይ ለማዋል የነበረውን ምኞትና ፍላጐት ይተርካል፡፡ ወጣቱ <u>አግዐዚ</u> (የታሪኩ ባለቤት) በውጭ ሀገር ሆኖ የአገሩ በኢጣሊያ መወረር እጅግ በጣም ያስቆጨውና ያሳዝነው እንደነበር፣ ቀጥሎም የኢጣሊያ ከኢትዮጵያ መውጣትንና ድልን የሚያበስር ታሪካዊ ልብወለድ ነው፡፡*

# አደፍርስ

በዳኛቸው ወርቁ ተፅፎ በ1962 ዓ.ም. ለህትመት የበቃው ይህ መጽሐፍ በጊዜው የነበረውን የመኳንንቱንና የባላባቱን የአኗኗር ሁኔታ እንዲሁም ስለ ሃይማኖት በሰፊው ይገልጻል:: አደፍርስ (የታሪኩ ባለቤት) ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በመሆን ከአዲስ አበባ ወደ ባላገር በመሄድ በአንድ ላይ መኖራቸውን በመተረክ በከተማውና በባላገሩ መካከል ያለውን ከፍተኛ የአስተሳሰብ፣ የልማድና የመሳሰሉትን ልዩነቶች በጉልህ ያስረዳል::

# እሳት ወይ አበባ

ይህ አንጋፋው ዕውቅ ባለቅኔና ደራሲ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን በ1966 ዓ.ም. ለሕመት ያበቁት የግጥም መድብል ነው:: ደራሲው በመፅሐፋ ውስጥ ስለ አካባቢዎች ስለ ኑሮ፣ ስለ ሰው ልጅ ስብዕና፣ ስለወንዞች፣ ስለ ዕውቅ ሰዎች ስለ ዕውነትና ውሸት፣ ስለ በዓላት፣ ስለከተሞችና ታሪካዊ ቦታዎች፣ ስለትዝታ፣ ስለረሃብና ችግር፣ ስለ ሕይወትና ሞት፣ ስለማህበራዊ አኗኗር፣ ስለወንዞችና ተራሮች፣ ስለ ተፈጥሮ፣ ሰለ ሰዎች ባህላዊ አኗኗር፣ ስለ ከተሞች ስለ ሀገር ቤት ሰው ባህሪ፣ ስለተለያዩ ሰዎች ሰራዎች፣ ስለ አገር ወዳድ መሪዎች፣ ስለ ቆሎ ተማሪ (ተችግሮ መማር ውጤቱ ጥሩ ስለመሆኑ)፣ ስለሰዎች ሁለንተናዊ ባህርይ፣ ስለፀሎት፣ ስለውበት፣ ስለፍቅር፣ በአጠቃላይ ስለ ተፈጥሮ እና ሌሎችም የተለያዩ ጉዳዮች በተለያዩ ስልቶች ያሳዩበት የግጥም መድብል ነው::

# የተውኔት ጉባዔ

በደራሲ መንግሥቱ ለማ ተደርሶ በ1975 ዓ.ም. ለህትመት የበቃው ይኸው መጽሐፍ ደራሲው በሕይወት ዘመናቸው ደርሰው አዘጋጅተው ለሕዝብ ዕይታ ያቀረቧቸውን (ፀረ ኮሎኒያሊስት)፣ «ባለ ካባና ባለ ዳባ» እንዲሁም «ጠያቂ» የተሰኙትን ተውኔቶች አካቶ የያዘ ነው፡፡

በዘመን ቅደም ተከተል ተስተካክክሎ የተቀመጠውና ከፋሽስት ወረራ እስከ 1966ቱ አብዮት የነበረውን የሰላሳ ስምንት ዓመታት የኅብረተሰብ እንቅስቃሴ የሚያመለክተው መድብል የኢትዮጵያን ሕዝብ ሕይወት አንባቢ በተውኔት መነፅር ተመልክቶ ግንዛቤ እንዲጨብጥ ታስቦ የቀረበ ነው፡፡

# ከአድማስ ባሻገር፣

በበዓሉ ግርማ ተደርሶ በ1976 ዓ.ም. ለሕትመት የበቃው «ከአድማስ ባሻገር» የተሰኘው ልብወለድ መጽሐፍ መንፈሱ የላሸቀ ትውልድ ለራሱም ሆነ ለአገሩ ሳይበጅ ብኩን ሆኖ እንደሚቀር ይተርካል፡፡

# የታንጉት ምሥጢር

በብርሃኑ ዘሪሁን ተደርሶ በ1979 ዓ.ም ለሕመት የበቃው ይህ መጽሐፍ በታንጉት /በገብርዬ ባለቤት/ ዙሪያ እያጠነጠነ በቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት የነበረቻውን ኢትዮጵያ በልብ ወለድ መልክ የዘከረበት፣ በተለይም የአጼ ቴዎድሮስ ባሕሪዎችና የጦርነት ውሎች ጉልተው የሚታዩበት ታሪካዊ ልብወለድ ነው፡፡